# በኦጋዴን የሚፈጸመውን የዘር ማጥራት ወንጀል ሕዝቡ በጋራ እንዲያወግዝ ተጠየቀ — ከቬጋስ

ሀብታሙ አሰፋ (ከቬጋስ)

አቶ መለስ ዜናዊ በረሃ በነበሩበት ወቅት 1977 የአገራችንን ድርቅ ተከትሎ ደርግ ረሃቡን የትግራይን ህዝብ ለማጥፋት እንደ መሳሪያ እየተጠቀመበት ነው ያሉት ዛሬ በሳቸው ስልጣን በኦጋዴን ህዝቡን በማስራብና የሰብአዊ መብት ጥሰት በመፈፀም የዘር ማጥፋት እየፈፀሙ ነው ይህን በጋራ ልናወግዝና ለተራበው ወገናችን ልንደርስ ይገባል ሲሉ አቶ ኦባንግ ሜቶ ገለጹ።

አቶ ኦባንግ ሜቶ በላስቬጋስ ከተማ ማክሰኞ ነሐሴ 23 /2011 በከተማዋ የኢትዮጵያ ራዕይ ማህበር በረሃቡ ለተጠቁ ድጋፍ ማሰባሰቢያ በጠራው ስብሰባ ላይ በተገኙበት ወቅት እንደገለፁት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የተከሰተው ረሃብ እየተባባሰ የሂደውና ህይወት የሚጠፋው በተፈጥሮ ሳይሆን በአቶ መለስ ድርጊት መሆኑን ጠቁመዋል።

አቶ ኦባንግ ከዓመት በፊት ሂዩማን ራይት ዎች በአገራችን እነ አቶ መለስ የእርዳታ እህል ለፖለቲካ መጠቀሚያ እያደረጉ መሆናቸውን ቢገልፁም ሰሚ አለማግኘቱን አስታውሰው በቅርቡ የቢቢሲ ዘጋቢዎች ያረጋገጡት ሀቅ ያንኑ በመሆኑ ስርዓቱ ህዝቡን ሆን ብሎ ወደ ረሃብ እንደሚገፋ ያሳያል በአሁኑ ወቅት በኦጋዴን እየተደረገ ያለውም ይሄው ነው ብለዋል።

"በስብሰባው አዳራሽ አንድም የኦጋዴን ተወላጅ አላየሁም ነገር ግን ኢትዮጵያውያን በወገናቸው ላይ የሚፈፀመው የሰብአዊ መብት ጥሰትና ረሃብ ሳቢያ እንዲሞት እየተደረገ ያለውን ህዝብ ለመታደግ ተሰብስበዋል" ያሉት አቶ ኦባንግ አያይዘውም "ይህ **የአዲሲቷ ኢትዮጵያ** ምሳሌ ነው። ለአገራችንና ለህዝባችን ስንቆም ከየት ነህ ከየት ነሽ ሳይባል ዘርና ጎሳን ወደጎን አድርገን **በኢትዮጵያዊነታችን እንቁም ለሰብዓዊነት ቅድሚያ እንስጥ**" ብለዋል።

አገሪቱ እስከመቼ ነው በድርቅ የምትጠቃው ወገናችን እስከመቼ ነው የሚራበው? የሚለውን መጠየቅ ተገቢ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ኦባንግ ይህን ለመለወጥ በስልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ ለመለወጥ ጎሰኝነት አእምሯችንን መርዞ አገራችንን እየጠፉ በመሆኑ ይህን አስወግደን በአንድ ላይ ስንቆም ብቻ መሆኑን ገልፀዋል።

**ማንም ከየት ይምጣ ከየት አያገባኝም ያሉት አቶ ኦባንግ ከጎሳችን በፊት የተወለድነው በሰውነታችን በመሆኑ ሊከፋፍሉን የሚሞክሩትን የነ አቶ መለስ ሴራ ወደ ጎን በማድረግ የኢትዮጵያ ጠላት ጎሳ ወይም ቋንቋ አይደለም ጠላታችን አገዛዙ በሁላችንም ላይ ያንሰራፋው ግፍ ነው ሲሉ አሳስበዋል።**

የኢትዮጵያ ችግር መፍትሄ የሁሉም ኢትዮጵያዊ በመሆኑ በዘርና በጎሳ በሀይማኖት ሳቢያ ሳይለያዩ ለነፃነት በአንድ ላይ በመቆም ነው ብለዋል። **በኢትዮጵያ ታሪክ ህዝብ ራሱን ያስተዳደረበት ወቅት ባለመኖሩ የነበሩት የአገዛዝ ስርአቶች ለፈፀሙት ወንጀል ይህኛው ወይም ያኛው ብሔር ተጠያቂ ነው ማለት እንደማይገባ ገልፀው የተጨቆንነው ሁሉ በአገዛዞች እንጅ በአንድ ወይም በሌላ ብሄር አይደለም ስልጣን በያዘው ስርአት ነው በማለት ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ ግንባታ ሁላችንም ሊከፋፍሉን የሚሞክሩትን አስወግደን ወደፊት መመልከት ይገባናል ብለዋል።**

ስርአቱ ህዝቡን ለመከፋፈል ኢትዮጵያን ለማጥፋት መስራቱ ለምን ይገርማችሁዋል? ሲሉ ተሰብሳቢውን የጠየቁት አቶ ኦባንግ አያይዘውም በዚህ ልንገረም አይገባም። ኢትዮጵያውያን በአንድ የቆሙ እለት ያበቃለታል። አገዛዙ ኦሮሞን ሄዶ አማራ ከሚገዛችሁ እኔ እሻላለሁ አማራው ጋር ሲሄድ ኦሮሞን እያጥላላ ጋምቤላው ደቡብም ሄዶ ህብረተሰቡን በጋራ እንዳይቆም ማድረጉን ገልፀዋል።

በያዝነው ክፍለ ዘመን የሰው ልጅ ስለ ሰብአዊነት ይጨነቃል እኛ ስለ ጎሳችን እንጨነቃለን ለዚህ ጥፋት መለስን ብቻ ሳይሆን የእኛንም የፖለቲካ መሪዎች መውቀስ እፈልጋለሁ ያሉት አቶ ኦባንግ ባቡር በሺህ የሚቆጠር ሰው ያጓጉዛል ነገር ግን የባቡሩ መሪ አንድ ነው በማለት በተወሰኑ ሰዎች የስልጣንና የመግነን ፍላጎት መለያየታችንን ጠቅሰው መሪዎች በኢትዮጵያ ህዝብ ነጻ ፈቃድ እንዲመረጡ እንስራ በማለት **ሁላችንም ነፃ ካልወጣን ማናችንም ነፃ አይደለንም** ሲሉ አስረግጠው ተናግረዋል።

በስብሰባው ላይ ተሳታፊ የነበረ ወጣት ሮባ አቶ አባንግን አመስግኖ መጀመሪያ የተወለደው ሰው ሆኖ እንጂ በብሄሩ አለመሆኑን በመጥቀስ የአዲሲቱ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄን በአባልነት ለመቀላቀል መወሰኑን ገልጿል።

በእለቱ በከተማዋ የስራ ፀባይ ብዙ ሰዎች በስብሰባው ላይ በመቅረታቸውና ሌሎችንም ለማሳተፍ ባለ ሀምሳ ዶላር ትኬት ለሽያጭ ይፋ የሆነ ሲሆን በስበሳባው አዳራሽ ከተገኙ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ዶላር ተዋጥቷል።ይህን ገንዘብ ካዋጡት አምስት መቶ ዶላሩን ዶ/ር ሙሉጌታ ካሳሁን ሲሆኑ ህፃን ጃጋማ ባልቻ ቤተሰቦቹ ሰጥተውት ካጠራቀመው 50 ዶላር መለገሱ ተገልጿል።

ዶ/ር ሙሉጌታ ካሳሁን ስብሰባውን የጠራው የኢትዮጵያ ራዕይ ሊቀመንበር በስፍራው እንደገለፁት የአቶ መለስ የህውሃት አገዛዝ በአገራችን የተከሰተውን ድርቅ ተከትሎ በረሀብ የተጠቃውን ህዝብ ሀላፊነት በጎደለው መንገድ በተለይ በኦጋዴን በወገናችን ላይ እርዳታ በመከልከል እያካሄደ ያለው የዘር ማጥራት ወንጀል በመሆኑ ወገናችንን ልንታደገው የበኩላችንን ልናደርግ ይገባል ብለዋል።

እነ አቶ መለስ በ1977 ዓም የተከሰተውን ረሀብ ተገን አድርገው የትግራይ ህዝብ ከደርግ የእርዳታ እህል እንደይቀበል በማድረግ ወደ ሱዳን አጓጉዘው ለፖለቲካ መጠቀሚያ ያደረጉ መሆናቸውን አስታውሰዋል። በወቅቱ በጉዞ ላይ በረሀብ የረገፉትን የትግራይ ቤተሰብ ይቁረጠረው በማለት ለዚያ ህዝብ የተሰጣቸውን እርዳታ እህሉን ሸጠው ገንዘቡን ወስደው የህውሃት ጉባኤ ላይ ውስኪ ሲያፈሱ ፍሪዳ ሲቆርጡ የነበሩና ወገኔ ላሉት ያላዘኑ በጠላትነት ለፈረጁት እንዴት ሊያዝኑ ይችላሉ? በማለት የህዝብ በረሃብ መሞት ግድ እንደማይሰጣቸው ገልፀዋል።

የኢትዮጵያን ለም መሬት ለባእዳን መንግስታትና ኩባንያዎች ለሱዳን ለህንድ ለፓኪስታን ለአረቦች ለረጅም ጊዜ የአገሪቱ ጠላቶች አሳልፎ የሰጠ አገዛዝ መሆኑን ጠቁመው ስርዓቱን ምርጫን የማይፈራ ለህዝብ ድምፅ የማይገዛ በመሆኑ መንግስት ከህዝብ ሳይመነጭ ረሃብ ሊጠፋ ብልፅግና ሊኖር አይቻልም ብለዋል። የአቶ መለስ አገዛዝ ድርቁ በውጭ መገናኛ ብዙሃን ከመውጣቱ በፊት ህዝቡን ሶስት አመት ልንቀልብ የምንችልበት አቅም አለን ሲል ዋሽቶ ቆይቶ ለችግሩ አለም አቀፍ ተቋማትን መወንጀሉን በማስታቀወስ ለተራበው ወገናችን የአቅማችንን ማድረግ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

**በእለቱ በስብሰባው አዳራሽ በተደረገ ውይይት በከተማው የሚኖሩ ሁሉንም ኢትዮጵያውያን የእርዳታ አሰባሳቡ ተሳታፊ ለማድረግ የ50 ዶላር የሽያጭ ትኬት የተሰራጨ ሲሆን በስብሰባው አዳራሽ የተገኙት ራሳቸውን አምባሳደር አድርገው ዕርዳታውን ትኬት እየሸጡ እንዲሰበስቡ ሀላፊነት ተሰጥቷል። ከትኬት ሽያጩም ሆነ ከመዋጮ የተሰበሰበው በአንድነት ለህዝቡ እርዳታውን ለሚያደርሱ አለም አቀፍ የእርዳታ ሰጭዎች ከሆኑት ለአንዱ ሲሆን ገንዘቡ በምንም መንገድ እርዳታን ለፖለቲካ መጠቀሚያ ለሚያደርገው አገዛዝ እጅ አይገባም ተብሏል።** ዕርዳታው እንደተሰጠም ድርጅቱ የሚሰጠው ማረጋገጫ ለህ/ሰቡ በግልጽ እንዲያውቀው ይደረጋል ተብሏል።

የስብሰባው ተሳታፊዎች በመጨረሻም ባለ 12 ነጥብ የአቋም መግለጫ ያወጡ ሲሆን በውስጦም በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ለወገናቸው ለመድረስ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ፣ የአቶ መለስ አገዛዝ በኦጋዴን የእርዳታ ሰራተኞችና ጋዜጠኞች እንዳይገቡ ያደረገውን ክልከላ እንዲያነሳ፣ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽንና ሌሎች ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብትተሟጋቾች በክልሉ በመንግስት እየተፈፀመ ያለውን ኢሰብአዊ ተግባር እንዲያጣሩ፣ እርዳት ለፖለቲካ መጠቀሚያ መሆኑ እንዲቆም ኢትዮጵያዊያን ድምፃችንን በጋራ እናሰማ የሚሉ ጥሪዎች የሚገኙበት ሲሆን በመጨረሻም በስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ አርሶና አርብቶ አደሩን ከቀዬና ከእርሻ እያፈናቀለ ለውጭ ባለሀብቶች መሬት እየሸጠ በመሆኑ ከዚህ ተግባሩ ተቆጥቦ በድርቅና በረሃብ የተሰቃየውን ወገን ወደነዚህ አካባቢዎች መልሶ እንዲያቋቁም ጠይቀዋል።

ፍርሃትና በጭቆና ሰንሰለት የታሰረ ህዝብ ራሱን መመገብ ይቅርና ህልውናውንም ማቆም አዳጋች በመሆኑ ነፃነቱን ለማቀዳጀት በቃ በሚል መፈክር ስር ራሱን አደራጅቶ ለተባበረ ትግል እንዲነሳ ጥሪ አድርገዋል።